# በአብክመ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የ2015 ዓ.ም ዓመታዊ ፊዚካል ዕቅድ

ነሀሴ /2014 ዓ.ም

<u>ባህርዳር</u>

መግቢያ//……………………………………………………………………………………………1

ክፍል አንድ፡- የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የባለፉት ዓመት የተግባራት አፈጻጸም ትንተና

1.የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም፡- ………………………………..2

2. ከባለድርሻ /ከአጋር አካላት ጋር ተሳትፎና ቅንጅታዊ አሰራር አንጻር፡-……………………………….9

3. በአጠቃላይ ባለፈው አንድ አመት የእቅድ አፈጻጸም ጉዞአችን የተገኙ ውጤቶች፡-…………………10

ክፍል 2፡ -ራዕይ፣ተልዕኮ፣ እሴቶችእና የአሰራር መርሆዎች፣ የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች ፣ዓላማዎች፣ ግቦች እና ዋናዋና ተግባራት፡-……………………………………………………………………….……11

ግብ.1. የአመራሩንና የፈጻሚዎችን አቅም ማሳደግ፡-……………………………………13

ግብ.2. የተገልጋዮችን እርካታና አመኔታ ማሳደግ፡-……………………………………14

ግብ.3. የሃብት አጠቃቀምንና ውጤታማነትን 100% ማድረስ፡-………………………15

ግብ.4. እምቅ ሃብትን በመለየትና የተለየዉንሃብት በማስተዋዎቅ አቅም ያላቸዉን ባለሃብቶች በመሳብ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ማሳደግ፡-…………………………………………………………16

ግብ.5. ለአምራች ኢንዱስትሪዎችና ለሌሎች ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚውል የመሬት፣ የመሰረተ ልማትና የፋይናንስ አቅርቦትን ማሳደግ፡-…………………………………………19

ግብ.6. የአምራች ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የማበረታቻ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመደገፍ ወደ አፈጻጸም የመግባት አቅማቸውን ማሳደግ፡-…………..23

ግብ.7.የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አማካይ የማምረት አቅም ከ52% ወደ 60% ማሳደግ፡……………..24

ግብ.8. በአምራች ኢንዱስትሪዎች እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከሚገኙ ምርቶች የሚገኝ የኤክስፖርት ገቢን ማሳደግ፡-…………………………………………………………….…26

**መግቢያ//**

በሀገራችን ሆነ በክልላችን ውጤታማ፣ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ለማረጋገጥ ዕድገት ተኮር የሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮችን በማስፋፋት ሥራ አጥነትን ለመቅረፍና ለኢኮኖሚው ዕድገት ያላቸውን ድርሻ ከፍ ለማድረግ በሙሉ አቅማችንና በተደራጀ አግባብ የባለሃብቱን አመለካከት በመለወጥና አቅማቸዉን በማጠናከር በስፋት በጋራ መረባረብ ይኖርብናል፡፡ እንዲሁም ውስብስብ የሆኑ ችግሮችን በመፍታት እና አቅም በመፍጠር በዘርፉ ተግባራት ላይ የክህሎትና የቴክኖሎጂ አቅም ክፍተትን በመሙላት፣ የተሟላ የዕሴት ሰንሰለት ድጋፍ በማድረግ፣ በቂ የገበያ ትስስር በመፍጠር፣ የማምረቻ መሳሪያዎችን አቅርቦት ችግር በማቃለል ምርቶችን ዘመናዊ በሆነ አግባብ በዓይነትም ሆነ በብዛት እንዲሁም በጥራት የማምረት አቅም መፍጠር ትኩረት የሚያሻ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የተሟላ ግብዓት፣ ተገቢ መዋቅራዊ አደረጃጀት እንዲኖር በማድረግ የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባርን በፅናት በመታገል በክልላችን ተንሰራፍቶ የቆየውን ድህነት ስር ነቀል በሆነ መልኩ መቀየር ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ክልሉ ምቹ የሆነ የአየር ንብረት ያለው ፣ ለኢንዱስትሪው እምቅ ሃብትና የሚሰራ የሰው ሃይል ያለውም ክልል ነው፡፡ ስለዚህ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ያለፉትን የዕቅድ ዘመን አደረጃጀቱ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመሆን በክልል ደረጃ ተወስኖ ይሰራ የነበረውን በአሁኑ ሰዓት ራሱን ችሎ በማቋቋም በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ዳር የሚያደርስ አደረጃጀት በመፍጠር ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ስለዚህ የ2014 ዓ/ም የዕቅድ ዘመን ከተከናወኑ ስራዎች መካከል የተሳኩትን፣ በታቀደው ልክ ውጤት ያልተመዘገበባቸውን፤ በዕቅዱ የትግበራ ሂደት ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችንና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በዝርዝር በመገምገም፤ ላጋጠሙን ተግዳሮቶች የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ፤ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የተሰማራውን ባለሃብትም ሆነ የሚመለከታቸውን አጋር አካላት በማሳተፍ፤የውስጣዊና ውጫዊ የሁኔታዎችን ትንተና መሰረት በማድረግ የቀጣይ የ2015 ዓመታዊ ዕቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡
:

## ክፍል አንድ፡- የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የባለፉት ዓመት የተግባራት አፈጻጸም ትንተና

1. **የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም፡-**

1. **የቁልፍ ተግባር / የለውጥ መሳሪያዎች/ ግንባታ አፈጻጸም**

*የተቋማትን የማስፈጸም አቅም ለመገንባት የተያዩ የለውጥ መሳሪዎች ተግባራዊ በማድረግ ተቋምን የመለወጥ ጉዳይ የማያቋርጥና ከህዝብ ፍላጎትና የልማት ዕድገት ጋር እያደገ የሚሄድ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ትግበራው የአንድ ወቅት አጀንዳ ሳይሆን እየተጠናከረ እና ስርዓት እየሆነ ሊሄድ የሚገባው ነው፡፡ የለውጥ መሳሪያዎች አንዱ አንዱን የሚተካ ሳይሆን በተሳሰረ አኳኋን የሚተገበር ነው፡፡ በመሆኑም የለውጥ መሳሪያዎችን በማቀናጀት የመተግበር ጉዳይ እንደ አንድ አቅጣጫ ተይዞ በጥብቅ ዲሲፒሊን ሊተገበር የሚገባው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የመንግስት ተቋማትን የሰው ኃይል አደረጃጀታቸውንና አሰራር በማጎልበት የተጠናከረ አቅም እንዲፈጥሩ ለማድረግ በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም አማካይነት የተለያዩ የለውጥ መሳሪያዎች ሲተገበሩ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህ የለውጥ መሳሪያዎች ውስጥ የመሰረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ (BPR)፣ የውጤት ተኮር ስርዓት (BSC)፣ የዜጎች ቻርተር፣ የካይዘን አሰራር እንዲሁም እነዚህን አቀናጅቶ ለመተግበር የሚያስችለው የለውጥ ሰራዊት ግንባታ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡*

*በመሆኑም የቁልፍ ተግባራት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በግልጽ የምንረዳበት ወሳኝ ክፍል የሆነውን የለውጥ ሰራዊት መገንቢያ ስትራቴጃችን ነው፡፡ ይህ ክፍል የለውጥ ሰራዊቱን ለመገንባት የሚያስችል መለኪያዎችንም አካትቶ ይዟል፡፡ ስትራቴጅው በርካታ ፈፃሚዎቻችን ዘንድ ተገቢውን ግልጽነት ያልተያዘበት፣ በተግባር ለመለካትም የተደበላለቀ አስተሳሰብ የሚታይበት፣ የተግባሩን አፈፃፀም ለመለካትና የጠራ አቋም ለመያዝ የምንቸገርበት ዋነኛ ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም የለውጥ ሰራዊቱ ተገነባ የሚባለው መቸ ነው? መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው? የሚሉትን መሰረታዊ ጉዳዮች በሚገባ በመገንዘብ በየጊዜው የተሰሩ ስራዎችን ከባህሪ ብቃት ጋር በማጣመር እየገመገሙ ወጥነት ያለው አቋም ይዞ መምራት ተገቢ በመሆኑ በባለፈው ዓመት ከነችግሩም ቢሆን ስንተገብራቸው ቆይተናል፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የመለኪያ መገለጫዎች ለሁሉም የለውጥ ሰራዊት ሀይሎች የሚያገለግሉ የጋራ መለኪያ ሲሆኑ ባለን ተቋማዊ መዋቅር ማለትም ከክልል ጀምሮ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ አደረጃጀትና በየደረጃው የሚገኙ ፈፃሚዎች ከየራሳቸው የስራ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ የለውጥ ሰራዊትን መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ በባለፈውን ዓመት የተሰሩና የታዩ እጥረቶችና የነበሩ የተሻሉ እንቅስቃሴዎች በዝርዝር ለማየት ያክል፡-*

ሀ/ አመለካከት

አመለካከት በሰዎች ባህሪ ላይ በጎና አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳረፍ የሚችል፣ የለውጥ ሰራዊቱ መሰረታዊ መለኪያ ተብሎ የሚወሰድ ነው፡፡ የተስተካከለ አመለካት የያዘ አመራር፣ መንግስት ሰራተኛ፣ባለሃብት፣ አጋር አካላትና ህዝብ አካባቢን ክልልን ብሎም ሀገርን የኢንቨስትመንትን ኢኮኖሚያዊ እድገት በማፋጠን ወደተሻለ እድገት ለመውሰድ የሚሳነው አይሆንም፡፡ ስለሆነም አንድን የለውጥ ሰራዊት ቁመና በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመረዳት የአመለካከት ግንባታ ወሳኝ ቦታ ያለው በመሆኑ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በመመስረት እንዲመዘን ተደርጓል፡፡ ተልዕኮን የመገንዘብና የማወቅ ፣ የአመለካከት ጥራት መያዝና የስራ ታታሪነት ዋነኛወቹ ቢሆኑም ክልሉም ሆነ ተቋማት በነዚህ አመለካከቶች ባለመቃኘቱ ለረጅም ጊዜ ለኢቨንስትመንቱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር አልተቻለም ፡፡ ስለሆነም በተቋማችን የአመራሩ ቁርጠኝነት እና የባለሙያው የስራ ተነሳሽነት ማነስ፣የተሰራውን ተቋማዊ አደረጀጀት ከስራ ማሳለጫነቱ ይልቅ የፖለቲካና የጥቅም ማግኛ አድርጎ የመጠበቅ ዝንባሌ በመታየቱ፣ባለሃብቶች ወደ ክልሉ መጥተው በማልማት የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት አልተቻለም፡፡

**ለ/ ክህሎት፤**

ክህሎት ሲባል በስልጠና (training)፣በልምድ (Experience) ወይም በተግባር የሚገኝ አንድን ነገር የማድረግ ወይም የመፈፀም ችሎታን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ክፍል ለማየት የተፈለገው በዋናነት ሶስት የለውጥ ሰራዊት መገንቢያ መለኪያ አቅጣጫ የሆኑ የማቀድ ችሎታ ፣ የተዘጋጀው እቅድ ከፈፃሚዎች ጋር መግባባት፣ እንዲሁም በየደረጃውና በየተቋማቱ የሚካሄደውን ድጋፍና ክትትል ስርዓት የሚመለከት ይሆናል፡ ፡ በመሆኑም ከላይ እስከታች ድረስ የሚገኙና እቅድ ማዘጋጀት የሚገባቸው ሀይሎች የየራሳቸውን እቅድ ማዘጋጀት አለመቻላቸው፣ የተዘጋጀው እቅድ የበላይ አካልንና የራስን አካባቢያዊ አቅም ያገናዘበ አለመሆንና ሁሉም ፈፃሚዎቻችን የአስተሳሰብ ግልጽነት፣ ተነሳሽነትና መግባባት አለመፍጠር እንዲሁም በእቅዳቸውም መሰረት ሪፖርት ማዘጋጀት በዘለለ፣ ግብረ- መልስ መስጠት፣ የተግባሮችን አፈፃፀም በአካል መመልከት፣ ምርጥ ልምድ መቀመርና ማስፋፋት፣ የስራ አፈፃፀም ላይ ተመስርቶ የሚካሄድ ግምገማ፣ ሂስና ግለሂስ፣ ደረጃ ምደባ እንዲሁም በየደረጃው የሚገኘውን አመራርና ተቋም አፈፃፀም የተቀራረበ እንዲሆን ለማስቻል የቴክኔካል ክህሎት ስልጠናና የድጋፍና ክትትል ስርዓት በጥልቅ በክህሎት መስራት አለመቻሉ፡፡

## ሐ/ አደረጃጀት

የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ አደረጃጀትን በማጥናት በ12 ዞኖችና በ3 ሜትሮፖሊታን 3 ጅኦ ሜትሮፖሊታን ከተሞች በ36 ከተሞችና በ93 የገጠር ወረዳዎች በጽ/ቤት ደረጃ የተደራጀ ሲሆን የለውጥ ስራዊት አደረጃጀት ከተቋሙ የበላይ አመራር የሚጀምር ነው። ሁለተኛው የሰራዊቱ አደረጃት የተቋሙን የማኔጅመንት ካውንስል የሚመለከት ነው። በሶስተኛ ደረጃ የሚኖው አደረጃት የሰራተኞች አደረጃት ሲሆን ሰራተኞችም በልማት ቡድን ወይም በአንድ ለአምስት አደረጃጀት ተፈጥሯል። ነገር ግን ባለፉት አንድ ዓመት የእያንዳንዱን አባል የአመለካከት፣ የክህሎትና የአሰራር ክፍተት በቀላሉ በመለየት ለመደገፍና በርካታ ግንባር ቀደሞችን በመፍጠር የመፈፀም አቅምን ለማጎልበት የሚያስችለው አደረጃጀት በመፍጠር የኢንቨስትመንቱን ችግር በሚፈለገው ደረጃ ለመፍታት ውስንነት ነበረው።

### መ/ አሰራር

ተቋሙ የሚመራባቸው አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እንዲሁም ሌሎች የአሰራር ሰርዓቶች ተዘርግተው ግልፅነትን የሚፈጥሩ ፣ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ሁነው መዘጋጀታቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። በየመስሪያቤቱ የተዘጋጁ አሰራሮችም ለተጠቃሚው ግልፅ ሆነው መቀመጣቸውም በተገቢው ሁኔታ ስራ ላይ ለማዋል ያስችላል። ስሆነም የለውጥ ሰራዊት የሚመራባቸው አሰራሮች የሚገኙበትን ሁኔታ በተግባር እየፈተሹ ማጠናከር ይገባል።ያሉትን አሰራሮች በማስገንዘብ ባለሃብቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ የተከናወኑ ስራዎች እና የአሰራር ማነቆዎችን ለመቅረፍ የተለያዩ የአሰራር ማናሎች ተዘጋጅተዋል። ነባሮችን ጨምሮ በአዲስ ለተመደቡ ሙያተኞችና አመራሮች ከኢንዱስትሪ ፖሊሲ እስከ ማስፈፀሚያ የአሰራር ማኗሎች ድረስ በአሉ የማስፈፀሚያ ህጎችና አሰራሮች ላይ የግንዛቤ ፈጠራ ስልጠና ሰጥቶ ወደ ስራ ማስገባት መቻሉ፣ በአጠቃላይ ከአሰራር አንጻር ሲታይ ለባለሃብቱ ግልጽ የሆነ አሰራር ዘርግቶ ውጤታማ ስራ በመስራት በኩል በአጋር አካላት፣ በአመራሩ እንዲሁም በባለሞያው በኩል ሰፊ ክፍተት አለ።

### ሠ/ ግብዓት

የግብዓት አቅርቦት ዓመታዊ ዕቅድና ግብ ለማሳካት የሚያችል ወሳኝ ነገር ነው። ግብዓት በሰው ሀይል፣ በቴክኖሎጅ ፣ በገንዘብና በቁሳቁስ መልክ የሚቀርብ ሲሆን በሚፈለገው ፍጥነት፣ ጥራትና መጠን መቅረብ ካልተቻለ ደግሞ ተግባራት እንዳይሳኩ ተግዳሮት ሆኖ በማገልገል ትልቅ ድርሻ አለው። ስለሆነም የለውጥ ሰራዊቱ ሲለካ የግብዓት አቅርቦቱ በሚፈለገው ፍጥነት፣ ጥራትና መጠን ባይባልም በተሻለ ደረጃ ለመፈፀመም ያስችላል።

በአጠቃላይ ሲታይ የለውጥ መሳሪያዎችን በልማት ሰራዊት ግንባታ በማስተሳሰር ስራችን በሚገባዉ ደረጃ ላይ ደርሷል ባይባልም ከነበረው አደረጃጀት አንጻር እና ከተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት አኳያ

ከነውስንነቱም ቢሆን በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ነገር ግን በታታሪነት መኳደልና ከኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብና ተግባር መውጣት ባልቻሉ አመራሮችና ፈጻሚዎች ምክንያት ዛሬም እንደትናንቱ የመልካም አስተዳደር ችግር ያለባቸዉ ወገኖች አልጠፉም፡፡ ስለዚህ ከችግሩ ለመውጣት በሚቀጥለው የእቀድ ዘመን ለአመራሩና ፈጻሚዉ በማያቋርጥ መንገድ ክህሎቱን የሚያሳድግ ስልጠና መስጠት የማይታለፍ ተግባር መሆንም አለበት፡፡

የተግባር አፈጻጸማችን ቀልጣፋና ዉጤታማ እንዲሆን ለማድረግ አሁንም ግልጽ አሰራር ሊቀመጥላቸዉ የግድ በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ መመሪያዎችን አዉጥቶ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም በተለያየ ጊዜ ተዘጋጅተዉ ለተግባር ማስፈጸሚያነት በተቋሞቻችን እጅ ላይ ባሉት የተለያዩ መመሪያዎች ላይ የበለጠ ግልጽነት እንዲፈጠርባቸዉ ማድረግና የተፈጻሚነት ደረጃቸዉ ምን እንደሚመስል በመከታተል ሊታረም የሚገባዉን ማረምና መመሪያዎቹ የተግባር መሳሪያ እንዲሆኑ ማድረግም ያስፈልጋል፡፡ ተግባራትን በተበተነ መንገድ በመምራት ዉጤታማ መሆንም አይቻልም፡፡ በመሆኑም በየደረጃዉ የፈጠርናቸዉን አደረጃጀቶች በሚፈለገው ልክ ለመስራት የሚያስችሉ በአለመሆናቸው አሁንም ቢሆን የተዘረጉ አደረጃጀቶችን በመፈተሽና በእውቀት ላይ የተመሰረተ የሰዉ ኃይል እንዲሟላና ምቹ የስራ ቦታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍም የሚሰማሩ ባለሃብቶቻችን ቁጥር በየዓመቱ እያደገ ከመሄዱ ጋር በተያያዘ አሁን ያለውን የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር የአሰራር አዋጅ በመፈተሸ መሬትን ዘመናዊና ልማታዊ በሆነ መንገድ መምራት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ቴክኒካል የአቅም ክፍተትን በመሙላት ለኢንዱስትሪው ምርታማነትን የሚያግዙ የመሰረተ ልማት ማነቆዎችን በመፍታት የአሰራር መመሪያዎች ስለሚያስፈልጉ ለአምራች ኢንዱስትሪዎቻችን መስፋፋት አዋጆችንና የአሰራር መመሪያዎችን እየፈተሹ መምራትን ይጠይቃል፡፡

## 2. በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ

ክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ አይነት ፀጋዎች እንዳሉት ይታወቃል፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ አካባቢ ያለውን ሀብት መሰረት አድርጎ በየትኛው ዘርፍ ቅድሚያ ሰጥቶ መስራት እንዳለብን የሚያመላክት ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ የትኩረት ዘርፎችንና አካባቢዎችን/ቦታዎችን በ6 ዋና ዋና ቀጠናዎች የለየ 1 የክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትምንት ፍኖተ-ካርታ የመጀመሪያ ድራፍት ተዘጋጅቷል፡፡

የክልሉን ምቹ ሁኔታና የሃብት አማራጮች በማስተዋወቅ ያለፈውን አንድ ዓመት በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ሥራዎች ክልሉን ዋነኛ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግ ዘመናዊና ውጤታማ ፕሮሞሽን ስልቶችን በመጠቀም የክልሉን የኢንቨስትመንት ገፅታ፣ አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎችን ለማስተዋወቅ ሆነ

ለመገንባት የሚመለከታቸውን አካላትና ባለሀብቶች በተደጋጋሚ 14,239 ባለሃብቶችና ለሌሎች የህ/ሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

የተለያዩ የፕሮሞሽን ስራዎች በመሰራቱ ለባለሃብቶች የምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም ወደ አፈጻጸም የሚገቡ ፕሮጀክቶችን በመለየትና በማስተዋወቅ 3,077 ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ምቹ ሁኔታ ከተፈጠረላቸዉ ባለሀብቶች ውስጥም ከፍተኛ ትኩረት አቅጣጫ የሆነውን የአምራች ኢንዱስትሪዎች 1,890 እና የቱሪዝም ኢንዱስትሪዎች 303 የተሰሩ ስራዎች ናቸው ፡፡ በተለያየ መንገድም ሆነ የፕሮሞሽን ስራ ተሰርቶላቸዉ ለ2,872 ባለሀብቶች የኢንቨስታመንት ፈቃድ መስጠት ተችሏል፡፡

በተደረገው ሁለንተናዊ ድጋፍና ክትትል የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን አቅም በማሳደግ ወደ አፈፃፀም የገቡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን 393 እነዚህም ፕሮጀክቶች ወደ ስራ የሚገባ ካፒታል መጠን በሚሊየን 11.4288 ብር ሲሆን ምርታቸውን ወደ ውጭ የላኩ አበባና አትክልት ፍራፍሬ ፕሮጀክቶች 3 ሲሆኑ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች 4,523.02 ቶን መላክ ተችሏል፡፡

**ኢንዱስትሪዎችን ከማበረታቻ ስራዎች አንጻር፡-** ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ለባለሃብቱ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች አንዱ ከጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ማበረታቻ ተጠቃሚ በማድረግ የኢንቨስትመንት አቅማቸውን በማሳደግ የባለሃብቶችን ውጤታማነት ከፍ ማድረግ ዋናው ተግባሩ ነው፡፡ በመሆኑም አገልግሎቱ ያገኙ የማበረታቻ መስፈርቶችን/ቅድመ ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ የሚጠበቅባቸውን መረጃዎች አሟልተው ለመጡ 248 ባለሃብቶች/ፕሮጀክቶች አገልግሎቱን አግኝተዋል፡፡ የጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ማበረታቻ አገልግሎቱን ፈልገው የመጡ ፕሮጀክቶች አናሳ የሆነበት ምክንያት በአሰራር መመሪያው መሰረት መረጃ አሟልተው ባለማቅረባቸው ሲሆን ከገቢ ግብር ከቀረጽ ነጻ ማበረታቻ ደግም ከላይኛዉ እስከታችኛዉ አደረጃጀት ድረስ ለባለሀብቶች የመጠቀም መብታቸዉን በማሳወቅና ግንዛቤ በመፍጠር እና በክትትልም በመደገፍ በኩል ያለው አፈጻጸም አናሳ በመሆኑ ተጠቃሚነታቸው ላይ አነስተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ባለሃብቶችን የሚያበረታታና የተሻለ አቅም ኑሯቸው ወደ ተግባር ለመግባት የሚስችል ዘርፍ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ የኢንቨስትመቱ ፍሰት ሲታይ በሚፈለገው ልክ የኢኮኖሚ ሽግግር ሊፈጥር የሚችል አምራች ኢንዳስትሪ በብዛት በማቋቋም ችግር ፈች የሆነ የስራ እድል ፈጠራ ስራ መስራት ባይቻልም የኢንቨስትመንት ፍሰቱ በቁጥር ሲታይ ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱና አዳዲስ ባለሃብቶች ወደ ክልሉ እንዲመጡ ፍላጎት ማሳደሩ እንደ ጥሩ ጅምር የሚታይ ነው፡፡ይሁን እንጅ ኢንቨስትመንትን ከመሳብና ወደ አፈፃፀም ከማሸጋገር

አኳያ የታዩ ችግሮች፡- የኢቨስትመንት ፕሮጀክቶች መረጃ ተለቅሞ በትክክል አለመያዝ ፤ባለሃብቱን ፕሮሞት በማድረግ ለመሳብ ምቹ ሁኔታዎች አለመኖር/ ባለሃብቱ እንደመጣ መሬት የማቅረብ ችግር፣የሃይል አቅርቦት ችግር፣የፋይናንስ አቅርቦት ችግር፣ የመንገድ፣የውሃ ወዘተ መሰረተ ልማት ችግሮች መኖር/፣ በክልሉ የፕሮሞሽን ስትራቴጂ አለመኖሩ፣ በዘረፉ የተሰማራው ባለሙያ የአካባቢውን ፀምቅ ሃብት አውቆ በበቂ ዕውቀትና ክህሎት ላይ ተመስርቶ አለማስተዋወቅ፣ በውጤት ሳይሆን በቁጥር ላይ የታጠረ ፕሮሞሽን መስራት፣ ልማታዊ የሆነውንና አቅም ያለውን ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር የኢኮኖሚ ለውጥ ሊያመጣ የሚችለውን ባለሃብት ለይቶ የማስተዋወቅ ስራ አለመስራት፣ለማስተዋወቅ ስራው አስፈላጊ ቁሳቁሶች በበቂ ሁኔታ አለመቅረብ፣ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚያስችሉ የፕሮሞሽን ዘይቤዎችን አለመከተል፣ በግብርና እና በአገልግሎት ሰጭ ዘርፎች ተሰማርተው ውጤት ያመጡ የአካባቢ ባለሃብቶችን አልሞ ወደ አምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ እንዲገቡ የማድረግ ስራ አለመስራት፣ ዘመናዊ የሆነ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን (ድህረ-ገፅ፣ ቋሚ የሚዲያ ፕሮግራም፣ ወዘተ…) ተጠቅሞ በማስተዋወቅ ረገድ ያልተሰራ ስራ መሆኑ፣ለባለሀባቱ አገልግሎት የምንሰጥበት ሂደት የተንዛዛ መሆን/**የአንድ ማዕከል አገልግሎት አለመኖር**/ እንዲሁም የበላይ አመራሩ ስትራቴጂክ በሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች የማስተዋወቅ ስራ አለመስራቱ የዘርፉን ዕድገት በሚፈለገው ደረጃ እንዳይደርስ ተግዳሮት የሆነ ስለሆነ በቀጣይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን ይጠይቃል፡፡

### 3. ከአምራች ኢንዱስትሪዎች አንጻር

➢ አዲስ ወደ ማምረት የገቡ ኢንዱስትሪዎች ወቅታዊ ማድረግ 102 (አነስተኛ 35 ፣መካከለኛ 32፣ ከፍተኛ 35 ) ፕሮጀክቶች መረጃ ወቅታዊ ተደርጓል፡፡

**በዘርፍ ሲታይ፡-**

- ✓ አግሮፕሮሰሲንግ 56 ( አነስተኛ 22፣ መካከለኛ 18፣ ከፍተኛ 16፣
- ✓ ኬሚካል/ኮንስትራክሽን 20 ( አነስተኛ 4፣ መካከለኛ 5፣ ከፍተኛ 11፣
- ✓ ጨርቃጨርቅና አልባሳት 14 ( አነስተኛ 7፣ መካከለኛ 2፣ ከፍተኛ 5፣
- ✓ ብረታብረትና እንጨት 12 ( አነስተኛ 2፣ መካከለኛ 7፣ ከፍተኛ 3፣

**በዚህ ተግባር የታዩ እጥረቶች፡-**

○ በዚህ ዘርፍ ፕሮጀክት ቀርጸው ቦታ የተሰጡ ባለሀብቶች ግንባታቸውን በአጭር ጊዜ አጠናቀው ወደ ማምረት እንዲገቡ ከክልል ጀምሮ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ያለው ባለሙያና አመራር በጥብቅ ዲሲፕሊን ያለመምራት፡፡

○ ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገሩትንና በተለያዩ ምክንቶች ወደ መረጃ ቋት ያልገቡ አምራች ኢንዱስትሪዎችን አዲስ ወደ ማምረት እንደገቡ አድርጎ መላክ፡፡

○ አዲስ ወደ ምርት የገቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች የደረጃውን መስፈርት ሳያሟሉ የመላክ በተለይም የሰው ኃይሉ ሳይሟላ በካፒታሉ ብቻ ደረጃ የመስጠት፡፡

○ የስራ ዕድል የተፈጠረላቸውን በወጣቶችና የአካል ጉዳተኛ መረጃ ለይቶ ያለማሳወቅ፡፡

➢ ነባር ኢንዱስትሪዎች መረጃቸውን ወቅታዊ ማድረግ የ3424 (**አነስተኛ 2450፣መካከለኛ 718፣ከፍተኛ 256**) አምራች ኢንዱስትሪዎችን መረጃ ወቅታዊ ለማድረግ ተችሏል፡፡

**በዘርፍ ሲታይ፡-**

✓ በአግሮ ፕሮሰሲግ ነባር ኢንዱስትሪዎችን ወቅታዊ ለማድረግ 753 (አነስተኛ 438 ፣መካከለኛ 214፣ ከፍተኛ 101) ወቅታዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

✓ ኬሚካል /ኮንስትራክሽን ልማት ነባር ኢንዱስትሪዎችን ወቅታዊ ማድረግ 321(አነስተኛ 136፣መካከለኛ 114 ፣ከፍተኛ 71) ወቅታዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

➢ ጨርቃጨርቅና አልባሳት ነባር ኢንዱስትሪዎችን ወቅታዊ ለማድረግ ታቅዶ 830 (አነስተኛ 740፣ መካከለኛ 53፣ከፍተኛ 37) ወቅታዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

➢ ብረታብረትና እንጨት ነባር ኢንዱስትሪዎችን ወቅታዊ ለማድረግ 1520 (አነስተኛ 1136፣መካከለኛ 337፣ከፍተኛ 47) ወቅታዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

➢ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ችግሮች በጥናት መለየት የ**1175** (አነስተኛ 863 ፣መካከለኛ 225፣ ከፍተኛ 87፣ አምራች ኢንዱስተሪዎችን ችግሮች ከተለዩትም ውስጥ የኢንዱስትሪዎችን ችግር መፍታት 1009 (አነስተኛ 750፣ መካከለኛ 186፣ የከፍተኛ 73) ኢንዱስትሪዎችን ችግሮች ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡

➢ ኢንዱስትሪዎችን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ በማድረግ የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ፣

- ✓ የኢንዱስትሪዎች የቴክኒካል ክህሎት ተጠቃሚ የሆኑ ለ1009 ኢንዱስትሪዎች፣
- ✓ የኢንዱስትሪዎች የኢንተርፕርነርሽፕ ተጠቃሚ የሆኑ 1268 ኢንዱስትሪዎች፣
- ✓ የኢንዱስትሪዎች የጥራትና ምርታማነት ተጠቃሚ 1267 ኢንዱስትሪዎች፣
- ✓ የኢንዱስት ሪዎችን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ 638 ኢንዱስትሪዎችን ፤

➢ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ሌሎች ድጋፎች ዋና ዓላማ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ምርት አምርተው ውጤታማ ለመሆን ችግር የሆነባቸውን ጉዳይ ለይቶ በመፍታት በሙሉ ዓቅማቸው እንዲያመርቱ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም በ2014ዓ/ም ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ወደ 68.5 በመቶ ለማሳደግ ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ቢሆንም እስካሁን ያለው ክንውን ግን የሚያሳየው 468( አነስተኛ 328 ፣ መካከለኛ 103 ፣ከፍተኛ

42 ) (ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅማቸው ያደገ ሲሆን በአራቱም ዘርፎች አማካይ የማምረት አቅም ሲወሰድ 67%) ላይ እንደሆነ ያሳያል፡፡ አፈጻጸሙም አነስተኛ ስለሆነ ወደፊት ጠንክሮ መስራትን ይጠይቃል፡፡

**2. ከባለድርሻ /ከአጋር አካላት ጋር ተሳትፎና ቅንጅታዊ አሰራር አንጻር፦**

አንቨስትመንት በጽንሰሀሳብ ደረጃ ሰፋ ያለ እና በኢኮኖሚ ደረጃ የገንዘብ መጠን እና የተቋም ድንበር የሌለዉ ቁሳዊ ሀብትን ስንመለከት ከሳንቲም ጀምሮ እልቆ መሳፍርት ወደሌለዉ የሀብት መጠን የሚያድግ የሚራባ የሚባዛ ሀብት ነዉ፡፡ በሴክተር ደረጃ ሲታይም በርካታ ተቋማትን የሚዳስስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋሪ የሚነካ ሁሉን አቀፍ ተቋም ነዉ፡፡ይሁን እና ሴክተሩን ለመምራት እንዲያመች ለማድረግ የራሱን የካፒታል ፣የተቋም አወቃቀር ወዘተ ወሰን ይዞ በህግ ወሰን ተበጂቶለት የሚሰራ ስራ ነዉ፡፡

ከላይ እንደተገለጸዉ ኢንቨስትመንት ሁሉን አቀፍ ቢሆንም በተቋሙ ላይ ጫና ያላቸዉ ተቋማት እንደተጽእኖ መጠናቸዉ በጎ እና አሉታዊ ተጽእኖ እያሳረፉ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ተቋማት መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት የመሰረተልማት አቅራቢ ተቋማት (መብራት ሀይል፣ መንገድ፣ ዉሀ እና ቴሌኮሙዩኒኬሽን) አበዳሪ ተቋማት (ልማት ባንክ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የግል ባንኮች ፣ኢንሹራነሶች ኢና የብድር እና ቁጠባ ተቋማት) መሬት አቅራቢ ተቋማት የገጠር መሬት አስተዳደር ቢሮ እና የከተማ ልማት ቢሮ፣ የግብርና ቢሮ፣ማህበራዊ ተቋማት ( የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ፣ጤና እና ትምህርት ቢሮ፣ዩኒቨርስቲዎች፣የምርምር ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ሴቶች)፣ አስተዳደርና ጸጥታ፣ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና የተለያዩ ሲቪክ ማህበራት ወዘተ….. ለኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ቁልፍ አጋሮች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተቋማት ለኢንዱስትሪው ውጤታማነት ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት የኢንዱስትሪዎችን ውጤታማነት ስናይ ከተለያዩ ችግሮች አንጻር በሚጠበቀው ልክ እንዳልሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህን አጋር ተቋማት በመያዝና ያለባቸውን ድርሻ በማሳየት የአሰራር ችግሮችን በመፍታትና በማስተካከል የኢንዱስትሪዎችን እድገት በሚፈለገው ልክ እንዲሆን መስራትን ይጠይቃል፡

3. በአጠቃላይ ባለፈው አንድ  አመት የእቅድ አፈጻጸም ጉዞአችን የተገኙ ውጤቶች

**1. በጦርነቱ ምክንያት ተፋዞ የነበረውን  የኢንቨስትመንቱን እንቅስቃሴ  የተለያዩ የንቅናቄ ስራዎችን በመስራት በተሻለ ሁኔታ እንዲነሳሳ መደረጉ፣**

- እስከታችኛው     ያለውን የዘርፉን መዋቅር  በመያዝ የ6 ወር እቅድ አፈጻጸምን በመገምገም ያልተፈፀሙ ተግባራትን በመለየት በየደረጃው ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የተሻለ ስራ መሰራቱ፣
- ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ያሉ ፕሮጀክቶችን በቅርበት በመደገፍና የታችኛው መዋቅር ፈጥኖ ወደ ስራ እንዲገባ መደረጉ፣
- ጥብቅ የድጋፍና ክትትል ስራ በመከተል ቢሮው በየሳምንቱ ለመምሪያዎች ተግባር ቆጥሮ የመስጠትና የመቀበል ስራ የተጠናከረ መሆኑ፣
- ከመምሪያዎች ጋር በ6 ወር እቅድ አፈጻጸም ግምገማ ላይ በመግባት የቴሌግራም የጋራ ቻናል በመፍጠር  በቢሮው ከፍተኛ አመራሮች በየሳምንቱ ለመምሪያዎች  የስራ እንቅስቃሰውን መሰረት ያደረገ የድጋፍ ግብረመልስ ሳይቆራረጥ የተሰጠ መሆኑ፣
- የባለድርሻ አካላትን ያሳተፉ ክልላዊ እና ዞናዊ መደረረኮች በተከታታይነት የተደረጉ መሆናቸው፣
- የኢትዮጵያ ታምርት የንቅናቄ መደረክና የ90 ቀን እቅድ በከፍተኛ ተነሳሽነት ከላይ እስከታች አጀንዳ ተደርጎ መሰራቱ፣

**4. የተለዩ ተግዳሮቶች/ችግሮች**

1. የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግር፣
2. የአበዳሪ ተቋማት የፋይናንስ አቅርቦት ችግር፣
3. የመሬት አቅርቦት ችግር፣
4. የፓወር/የኃይል አቅርቦት ችግር ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡
5. **የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ችግር፡-**

- ✓ የግብርና ግብዓቶችን ማምረት የሚያስችሉ እምቅ ሀብት ያለ ቢሆንም እነዚህን ግብዓቶች በማምረት በሚፈለገው ጥራት፣ ዋጋ፣ መጠንና ጊዜ ለኢንዱስትሪው ማቅረብ አለመቻሉ፤
- ✓ በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ ኢንቨስተሮች ለአምራች ኢንዱስትሪው ግብዓት የሚሆን ምርት ማምረት አለመቻለቸው፣
- ✓ በሃገር ደረጃ በተፈጠረው የውጭ ምንዛሬ እጥረትና ያለውንም የውጭ ምንዛሬ ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ትኩረት ባለመሰጠቱ በግብዓት አቅርቦቱ ዙሪያ ከፍተኛ ችግር መፍጠሩ፤

- ✓ የግብዓት እጥረቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከአቅም በታች እንዲያመርቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፤

ክፍል 2፡ -ራዕይ፣ተልዕኮ፣ እሴቶችእና የአሰራር መርሆዎች፣ የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች ፣ዓላማዎች፣ ግቦች እና ዋናዋና ተግባራት

2.1. ራዕይ፡- የክልሉ ኢኮኖሚ በኢንዱስትሪ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ማየት።

**2.2. ተልዕኮ፡-**

- ✓ የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማስፋትና የዘርፉን ማነቆዎች በመለየት ለመፍትሄ የሚረዱ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን በመቀመርምቹ የሆነ የኢንዱስትሪና የኢንቨስትመንት መሰረቱን በማስፋት የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ማሳደግ፣
- ✓ የክልሉን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ልማት የሚደገፉ ተቋማትን አቅም በመገንባትና በቴክኖሎጂ በመደገፍ የዘርፉን ፈጣን ልማትና ቀጣይነት ማረጋገጥና የክልሉን ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ማፋጠን፣
- ✓ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤት የሆኑ ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት መተካት፣
- ✓ አምራች ኢንዱስትሪዎችና የግብርና ኢንቨስትመንት የኤክስፖርት ምርትን በማምረት የገበያ ትውውቅ ሥራዎችን በማመቻቸት የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ፣
- ✓ በኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች ዘመናዊና ተወዳዳሪ የሆነ የአሰራር ስርዓትን ተከትለው የዘርፉን ልማት እንዲያስፋፉ በመደገፍ ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር፣ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ።

## 2.3. እሴቶችናየአሠራርመርሆዎች

- ✓ የላቀ አገልግሎት፣
- ✓ የደንበኛ እርካታ፣
- ✓ ጥራትና ቅልጥፍና፣
- ✓ የስራ ፍቅርና ከበሬታን፤
- ✓ አገልጋይነት፣
- ✓ ቅንጅታዊ አሰራር
- ✓ ዘመናዊነት
- ✓ ዝግጁነት

## 2.4. የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች

**ሀ) የፌደራል የበጀት አመቱና የ10 አመት እቅድ እንደመነሻ፣**

**ለ) የክልሉና አጠቃላይ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች**

- ✓ በትግበራ ላይ ያለው የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፤
- ✓ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ዘርፉ የሚመራባቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች፤
- ✓ ሌሎች የአሰራር ማዕቀፎች፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፤

**ሐ) የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ራዕይ እና ተልዕኮእንደመነሻ**

**መ) የክልሉ የተፈጥሮና ሰዉሰራሽ ሃብቶች ፣የቱሪዝም መስህቦች እና የግብርና ውጤቶች**

**ሠ)ያለፉት ዓመታት አፈፃፀሞች**

- ✓ የ2014 ዓ/ም በትግበራ ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች፣የተሻሉ አፈጻጸሞች እና ያጋጠሙ ችግሮች እንደመነሻ ተውስደዋል፤

## 2.5. የትኩረት መስኮች

1. **የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም**
2. **የአዳዲስ እና የነባር ኢንቨስትመንት መጠናከር፣**
3. **ጥናትና ምርምር**
4. **የቴክኖሎጅ ልማትና የመረጃ ስርዓት ዝርጋታ**

## 2.6. የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች

1. በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ቀዳሚ ሚና እና ትስስር ተመስርቶ በክልሉ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲመጣ ለማስቻል ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ መፍጠር፣
2. ዘላቂ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ እና የዜጎችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ዘርፎችን በብዛት እና በጥራት ወደ ክልሉ መሳብ፣
3. የአምራች ኢንዱስትሪ እና የሌሎች ኢንቨስትመንት ዘርፎችን ቀጠናዊና የእሴት ሰንሰለት ትስስር በማጠናከር የማምረት አቅማቸውን በማሳደግ፣ እና ተወዳዳሪነታቸውን በማጠናከር ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግ፣
4. የአገልግሎት እና የግብርና ዘርፍን ኢንቨስትመንት በማስፋፋትና ተወዳዳሪነታቸውን በማጠናከር ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግ፣
5. የተቋሙን የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም በማጎልበት እና በቅንጅታዊ አሰራር በክልሉ ተገልጋይ ተኮር የኢንቨስትመንት አገልግሎትን በማስፈን የኢንቨስትመንት እድገት ማረጋገጥ፣

2.7. ዓላማ፡- ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ውጤታማ ለማድረግ የ2015 በጀት አመት እቅዱን በ3 ዓለማዎችና በ12 ግቦች በማደራጀት እንዲሁም ዋና ተግባራትንና ዝርዝር ተግባራትን በመለየት አላማዎችን ከግብ፣ከዋና ዋና ተግባርና ዝርዝር ተግባራት ጋር ቀጥሎ በተቀመጠው አግባብ በማስተሳሰር እቀዱን አዘጋጅቷል፡-

**ዓላማ.1.** በየደረጃው የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን በመገንባት የኢንቨስትመንቱን እድገት ማረጋገጥና ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማጠናከር የተቋሙን ተልዕኮ ማሳካት፣

**ዓላማ.2.** ክልሉን ተወዳዳሪ እና የተሻለ የኢንቨስትመንት መዳረሻ በማድረግ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በማስፋፋትና በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ/ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ በማሳደግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

**ዓላማ 3**፡- ለአምራች ኢንዱስትሪው እና ለሌሎች ኢንቨስትመንቶች አገልግሎት የሚውል የመሬት እና ሌሎች መሰረተ-ልማት አቅርቦትን በማሟላት፣ ለኢንዱስትሪዉ ጥሬ ዕቃ በማቅረብ የተሻለ የእሴት ጭማሪ ያላቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች በብዛት፣በጥራትና በዓይነት በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት የሚችሉ አምራች ኢንዱስትሪዎችን እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በማደራጀት እንዲስፋፉ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል፤

## ግብ.1. የአመራሩንና የፈጻሚዎችን አቅም ማሳደግ፡፡

### 1.1. የስልጠና ክፍተትን መሰረት በማድረግ ስልጠናዎችን በመለየት ስልጠና መስጠት፤

- 8 የተለያዩ የስልጠና ፍላጎቶችን/ ክፍተቶችን መለየት፣
- በተለያዩ 22 አይነት ስልጠናዎች ለ290 ለተቋሙ አመራሮች እና ለ566 ባለሙያዎች በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍና በሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት
- ለ 20 አማራሮችና ባለሙያዎች የረጅምጊዜ ስልጠና መስጠት፣
- ለ294 አመራሮችና ባለሙያዎች በቢሮው የሚተገበሩ ሶፍት ዌሮችን አጠቃቀም በተመለከተ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት፣
- የተሰጡ ስልጠናዎችን መሰረት በማድረግ ስልጠናዎች ያስገኙትን ውጤት መገምገም

### 1.2. የርዕስ በርዕስ የመመማሪያ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣

- በተዋረድ በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የመመማርያ ሰነዶችን በማዘጋጀት በየወሩ ወራዊ የመመማሪያ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣

1.3 የማኔጅመንትና የልማት ቡድን አደረጃጀቶችን ማጠናከር

- **የበጀት አመቱን ዕቅድ በጥራት ማዘጋጀት፣ ተግባራትን በየሳምንቱ፣ በየወሩና በየሩብ ዓመቱ እየገመገሙ መምራት**
- **በዞኖች፣ በከተሞችና በወረዳዎች መካከል ያለዉን የአፈጻጸም ልዩነት ለማጥበብ ተከታታይነት ያለዉ ድጋፍና ግብረ-መልስ መስጠት፣ የመጣዉን ለዉጥ መለካት**

## ግብ.2. የተገልጋዮችን እርካታና አመኔታ ማሳደግ:-

2.1. **የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ማዘጋጀትና በስታንዳርዱ መሰረት ተፈጻሚ ማድረግ፣**

- በተዋረድ ባሉ ተቋሞቻችን የኢንዱስትሪንና ኢንቨስትመንትን ተግባርና ኃላፊነት የሚመጥኑ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ማዘጋጀት፣
- የተቋሙን ተግባርና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ የተዘጋጀውን የአገልግሎት አሰጣት ስታንዳር መሰረት በማድረግ የተሰጠውን አገልግሎት መተካት፣

2.2. **የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዱን ለተገልጋዮች ተደራሽ በማድረግ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት፣**

- ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት ሰፊ የኢንቨስትመንት ፍሰት ባለባቸው 5 ከተሞች (ባህርዳር፣ ኮምቦልቻ፣ ደ/ብርሃን፣ ጎንደርና ደ/ማርቆስ) የአንድ ማዕከል አገልግሎት የማቋቋም ስራ መስራት፣

2.3. **ጠቃሚ የሆኑ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል፣**

- የለማው ኢንቨስትመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም (ሶፍትዌር) አገልግሎት መስጠት ባልጀመረባቸዉ 60 የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋሞች እንዲተገበር ተደራሽ ማድረግ፣
- በአዲስ በለማው ድህረ ገጽ ላይ ለቢሮው ስልጠና በመስጠት ወደ ስራ ማስገባት፣
- እየለማ ያለውን የእቅድ ሪፖርት ክትትልና ግምገማ ሲስተም በማጠናቀቅ ከኢንቨስትመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተሙ ጋር ሊንክ ፈጥሮ እንዲመዝን በ123 ተቋሞቻችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- የኢንቨስትመንት ተቋሞች የኦን ላይን የኔት ወርክ ተጠቃሚ ማድረግና የተቋሙን የኔትወርክ ደንነቱን መጠበቅና መንከባከብ፣
- የድጋፍ ስራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል በሁሉም ተቋማት ያሉ ባለሙያዎችን በሲስተም አሰራር ላይ በማብቃት ሙሉ በሙሉ ስራቸውን በኦንላይን እንዲሰሩ ማድረግ፣

2.4. **ምቹና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያግዙ መመሪያዎችን፣ ማኗሎችንና ማሻሻያዎችን እንዳስፈላጊነቱ ማዘጋጀት፣**

- ምቹና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያግዙ 3 መመሪያዎችን በአዲስ ማዘጋጀትና 6 እየተሰሩባቸው ያሉ የአሰራር መመሪያዎችን ማሻሻል፣
- ምቹና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የሚያግዙ 3 የአሰራር ማኗሎችን እንዳስፈላጊነቱ ማሸሻል፣

2.5. **የኢንቨስትመንት ፈቃድና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚመጡ ባለሀባቶችን 100% አገልግሎቶችን መስጠት፣**

- ለ3000 ባለሃብቶች በኢዚኩ መሰረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ አገልግሎት መስጠት ፣
- ለ4217ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ፈቃድ ማደስ፣
- የለውጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሚፈልጉ ባለሃብቶች 100% አገልግሎት መስጠት
- ትክ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሚፈልጉ ባለሃብቶች 100% አገልግሎት መስጠት፣

2.6. **በእቅድ ዝግጅትና በእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ዙሪያ ባለድርሻ አካላትን መለየትና ማወያየት፣**

- በተዋረድ ባሉ የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋሞቻችን የሚመለከታቸውን 10 ባለድርሻ አካላትን መለየትና የጋራ መግባቢያ ሰነድ መፈራረም፤
- በጋራ የሚሰሩ ስራዎችን በመለየትና የጋራ እቅድ ማዘጋጀት፣
- በየሩብ አመቱ ቋሚ የግንኙነት ጊዜ በመወሰን በእቅድ ዝግጅትና በእቅድ አፈጻጸም ግምገማ የተከናወኑ ተግባራትን መገምገም፣

## ግብ.3. የሃብት አጠቃቀምንና ውጤታማነትን 100% ማድረስ፣

3.1. የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ 8 ሚሊዮን ተጨማሪ ሃብት በገንዘብ እና በቁሳቁስ እንዲገኝ ማድረግ፣

3.2. በሚገኘው ገቢ እና በተመደበው የመንግስት በጀት ተቋሙን 100% በሎጅስቲክስ እንዲሟላ ማድረግ፤

3.4. የተመደበውን የካፒታል በጀት 100% ለታለመለት ዓላማ ማዋል፤

3.5. በ2013 በጀት አመትና በ2014 በጀት አመት ለውሃ ጉድጓድ፤ ለመብራትና ለጠጠር መንገድ ግንባታ የተከፈለ በጀትን ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመነጋገርና በመከታተል ወደ ተግባር እንዲገባ ማድረግ፤

**ግብ.4. እምቅ ሃብትን በመለየትና የተለየዉን ሃብት በማስተዋዎቅ አቅም ያላቸዉን ባለሃብቶች በመሳብ የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ማሳደግ፤**

**4.1. የክልሉን ቀጠናዊ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ ዝርዝር ጥናት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር (በአማካሪ) በማስጠናት ወደ ስራ ማስገባት፡**

- የተለዩትን 6 የልማት ቀጠናዎች ከዩኒቨርስቲዎችና ከሚመለከታቸው ሌሎች አጋር አካላት ጋር በመተባበር ወይም በአማካሪ ጥልቅ ትንተና ጥናት ማጥናት፤
- ከጥልቅ ትንተናው በመነሳት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የክልሉ ኢንቨስትመንት አማራጮች መለየት፤
- ለእያንዳንዱ ቀጠና ያለውን ፀጋ/እምቅ ሃብት) መሰረት በማድርግ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ 6 የኢንቨስትመንት አማራጮች መለየት፤
- በእያንዳንዱ ቀጠና ቅድሚያ ለተሰጣቸው አማራጮች ቢያንስ 2 የኢንቨስትመንት አማራጭ ሃሳቦች የቅድመ አዋጭነት ጥናት ማስጠናት፤
- ከዚህ ቀደም ቅድመ አዋጭነት ጥናት የተሰራላቸውን 32 የፕሮጀክት ሃሳቦች ወቅታዊ ማድረግ፤
- እንደ ክልል እና እያንዳንዱ ዞን ቀጠናዊ የ10 ዓመት ፍኖተ ካርታዉን መሰረት በማድርግ የራሱን የኢንቨስትመንት ፀጋዎችና አማራጮች ወቅታዊ እንዲያደርግ ማድርግ

4.2. **በተመረጡና አዋጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ኢንቨስት የሚያደርጉ 4800 አቅምና ፍላጎት ያላቸዉን ባለሀባቶች ከተለያዩ ክፍሎች በመለየት መመልመል፤**

- 300 ነባር ኢንቨስተሮችን ዳግም ኢንቨስት እንዲያደርጉ ለይቶ መመልመል፤
- 4,320 አዳዲስ የሃገር ዉስጥ ባለሃብቶችን ለይቶ መመልመል ፤
- 107 ሐብት ያፈሩና ሞዴል አርሶ አደሮችን፤ሽግግር ያደረጉ ኢንተርፕራይዞችን መለየት,

- 50 ዲያስፖራዎችን ወደ ክልሉ መጥተዉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ በድረ-ገጽ እና በሌሎች አማራጮች መለየት፣
- 23 ታዋቂ የሆኑ የዉጭ ባለሃብቶች ወደ ክልሉ መጥተዉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ በድረ-ገጽ እና በሌሎች አማራጮች መለየት፣

### 4.3. የኢትዮጵያ ታምርት እና የተለያዩ የማስተዋወቂያ ዘዴዎችን (Promotion Strategies) በመጠቀም ከ10,000 በላይ የሚሆኑ የተለዩ ባለሃብቶችንና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የማሰተዋወቅና ገፅታ ግንባታ ስራ መስራት፣

#### 4.3.1. የገፅ ለገፅ የፕሮሞሽን ስልቶችን በመጠቀም የኢንቨስትመንት አማራጮችንና ምቹ ሁኔታዎችን የማስተዋወቅናየገፅታ ግንባታ ስራ ማከናወን

- 100 **የኢትዮጵያ ታምርት** እና የተለያዩ የኢንቨስትመንት ፎረሞችን በማካሄድ ከ10,000 ባለሃብቶችንና ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ማስተዋወቅ፣
- 30 ልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት ፓናሎችን በማካሄድ 3000 ኢንቨስተሮችና የህብረሰብ ክፍሎችን ማስተዋወቅ,
- የተለያዩ ባለሃብቶችና የህብረተሰብ ክፍሎችን ያሳተፈ 16 የመስክ ጉብኝት በማካሄድ የርዕስ በርዕስ ልምድ ልውውጦች እንዲገኙ በማድረግ ኢንቨስት እንዲያረጉ ማነሳሳት፣የገፅታ ግንባታ ስራ መስራት፣
- በተደረገውን የመስክ ጉብኘት መሰረት በማድረግና ሌሎች አስተማሪ ስራዎች ያሉባቸውን በመምረጥ 16 የተለያ አስተማሪ የሆኑ ተሞክሮችን በመቀመር ማስፋት፣
- በዞኖች፣ ከተሞችና ወረዳዎች 20 ባለሃብቱን መሰረት ያደረጉ የምርት ትዉዉቅ ባዛርና ኤግዚብሽን ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የገጽታ ግንባታ ስራዎችን መስራት፣

#### 4.3.2. ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን በመጠቅም ማስተዋወቅና የገጽታ ግንባታ ስራ ማከናወን

- 32 ጊዜ በተለያዩ የአገር ውስጥና የውጭ ኤሌክትሮኒክስ ሚድያዎችን ተጠቅሞ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎች ማስተዋወቅ (ዜና፣የስቱዲዮ ውይይት፣ Zoom conference...)
- በተለያዩ የሃገር ውስጥ ሚዲያዎች 10 ጊዜ ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲዘጋጅ በማድረግ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎች ማስተዋወቅ፣
- አንድ ዶክሜንታሪ ፊልም በማዘጋጀት የገጽታ ግንባታ ስራ መስራት፣

- መደበኛ የአየር ሰዓት በመግዛት በወር አንድ ጊዜ  የክልሉን ኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሀኔታዎች ማስተዋወቅ፣

### 4.3.3. የተለያዩ የህትመት ሜድያዎችን በመጠቀም የኢንቨስትመንት አማራጮችና ምቹ ሁኔታዎች ማስተዋወቅ፣ የክልሉን ገፅታ መገንባት

- በአይነት 40 በተለያዩ ርዕሰ ጉዳይዮች  500 ብሮሽሮችን  በማዘጋጀት ማሰራጨት፣
- 10,000 ባራሪ ወረቀቶችን በተለያዩ 52 ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በማዘጋጀት ማሰራጨት፣
- 525 መጽሔቶችን አሳትሞ ማሰራጨት,
- ለተለያዩ 5 የህትመት ሚድያዎች (ለጋዜጦች፣ለመጽሔቶች፣...) መረጃዎችንና አማራጮችን በመስጠት ማስተዋወቅ፣
- ከ30 በላይ የተለያዩ መልዕክቶች ያሏቸውን ባነሮች በማዘጋጅ የገፅታ ግንባታና የማስተዋወቅ ስራ መስራት፣
- 18 ቋሚና ተንቀሳቃሽ የተለያዩ የፎቶ ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት የኢንቨስትመንት አማራጮችን ማስተዋወቅ፣

### 4.3.4. የማህበራዊ ሜድያዎችን (ፌስቡክ፣ ዩቲዩብ፣ ቴሌግራም፣ ዋትሳፕ) በመጠቀም የኢንቨስትመንት አማራጮች ምቹ ሁኔታዎች ማስተዋወቅ ገፅታ መገንባት

- 1,200 ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳይ  መረጃዎችን በመጫን፣በማጋራት ኢንቨስትመንቱን የማስተዋወቅ ስራ መስራት፣
- ልዩ ልዩ መረጃዎችን በመጫንና በማጋራት አሁን ያለውን 15,625 የቢሮው የፌስ ቡክ ተከታዮች ቁጥር 17,000 በላይ ማድረስ፣

## 4.4. በተለያዩ ስልቶች የማስተዋወቅ ስራ ከተሰራላቸው ባለሃብቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ አቅም ያላቸውን ባለሀብቶች መልምሎ በተለያዩ ዘርፎች ኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያወጡ ማድርግ፤-

- 175 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡና በሙሉ አቅማቸው ወደ ስራ  ስገቡ ወንድ 212,503 ሴት 187,782 ድምር 400,285 ዜጎች ስራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ 3000 ባለሃብቶች በተለያዩ ዘርፎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች ፈቃድ እንዲያወጡ ማድረግ፣
- ፈቃድ የሚያወጡ ባለሃብቶችም 600 በአግሮፕሮሰሲንግ፣220 በጨርቃጨርቅና ቆዳ፣250 በኬሚካልና ኮንስትራክሽን 380 በብረታ ብረትና እንጨት፣340 በሆቴልና ቱሪዝም፣ 7 በአበባ፣

አትክልትና ፍራፍሬ፣ 320 በግብርና እና 883 በሌሎች የአገልግሎት ዘርፎች እንዲያወጡ አልሞ መስራት

**4.5. ለክልሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት ተግዳሮት ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮችን በመለየት እንዲፈቱ ማድረግ፡**

- ✓ የክልሉን ኢንቨስትመንት ማነቆዎች (ተግዳሮቶች) የለየና የመፍትሄ ሃሳቦችን የያዘ አንድ የጥናት ሰነድ ማዘጋጀት፣
- ✓ የክልሉን ኢንቨስትመንት የሚመለከቱ በማህበራዊ ሚድያዎችና በመደበኛ የመገናኛ ዜዴዎች የሚተላለፉ አፍራሽ /አሉታዊ እሳቤዎች/ እየተከታተሉ 100% ተገቢውንና ትክክለኛውን መረጃ ለህዝብና ለመንግስት መስጠት፣
- ✓ በየጊዜው ከመንግስትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የሚሰጡ የወቅታዊ አጀንዳዎች 100% ውይይት መደረኮችን በማዘጋጀት የቢሮውን ገፅታ የሚገነቡና መልካም ተግባቦትን የሚፈጥሩ ተግባራትን ማከናወን

## ግብ.5. ለአምራች ኢንዱስትሪዎችና ለሌሎች ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚውል የመሬት፣ የመሰረተ ልማትና የፋይናንስ አቅርቦትን ማሳደግ፣

**5.1. ለሁሉም አምራች ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች 3,809 ሄ/ር መሬት በ189 ከተሞች በሳይት ፕላንና በካርታ የተመላከተ ለአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል መሬት ማዘጋጀት**

- ➢ በ137 ከተሞች 2,630 ሄ/ር ለሁለገብ ኢንዱስትሪ መንደር/ፓርክ አገልግሎት የሚውል በሳይት ፕላንና በካርታ የተመላከተ መሬት ማዘጋጀት፣
- ➢ በ3 ከተሞች 900 ሄ/ር ለተቀናጀ ኢንዱስትሪ ፓርክ አገልግሎት የሚውል በሳይት ፕላንና በካርታ የተመላከተ መሬት ማዘጋጀት፣
- ➢ በ49 ከተሞች 279 ሄ/ር ከኢንዱስትሪ መንደርና ፓርክ ውጭ አገልግሎት የሚውል በሳይት ፕላንና በካርታ የተመላከተ መሬት ማዘጋጀት፣

**5.2. ለሁሉም ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች በሳይት ፕላን ከተመላከተው መሬት** በ112 ከተሞች 3,690.15 ሄ/ር **መሬት ከሶስተኛ ወገን የፀዳ እንዲሆን ማድረግ፣**

- ➢ በ58 ከተሞች ለሁለገብ ኢንዱስትሪ መንደር /ኢንዱስትሪ ፓርክ 2,858.65 ሄ/ር መሬት ከሶስተኛ ወገን ነጻ ማድረግ፣

➢ በ6 ከተሞች ለተቀናጀ ኢንዱስትሪ ፓርክ አገልግሎት የሚውል በሳይት ፕላንና በካርታ የተመላከተ 437 ሄ/ር መሬት ከሶስተኛ ወገን ነጻ ማድረግ፣
➢ ከኢንዱስትሪ መንደርና ፓርክ ውጭ ለሚቀርቡ ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል በ48 ከተሞች 328 ሄ/ር መሬት ከሶስተኛ ወገን ነጻ ማድረግ፣

**5.3. ከአምራች ኢንዱስትሪው ውጭ ለሆኑ ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መሬት በማዘጋጀት ከ3ኛ ወገን እንዲፀዳ ማድረግ፣**

➢ በግብርው ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ባለሃብቶች 15,570 ሄ/ር መሬት በመለየትና በሳይት ፕላን በማመላከት 12,618 ሄ/ር መሬት ከ3ኛ ወገን በማጽዳት ለባለሃብቶች ማዘጋጀት፣
➢ በአበባ፣አትክልት፣ፍራፍሬ እና ዕፀ-ጣዕም ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ባለሃብቶች 16,555ሄ/ር መሬት በመለየትና በሳይት ፕላን በማመላከት 13,455ሄ/ር መሬት ከ3ኛ ወገን በማጽዳት ለባለሃብቶች ማዘጋጀት፣
➢ በአገልግሎት ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ባለሃብቶች 3,000 ሄ/ር መሬት በመለየትና በሳይት ፕላን በማመላከት 2,050 ሄ/ር መሬት ከ3ኛ ወገን በማጽዳት ለባለሃብቶች ማዘጋጀት

**5.4. የሚቀርቡ የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን መገምገም፣**

➢ በአዲስ የቀርቡ 1,528 የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን መገምገም፣
➢ በአዲስ ለሚቀርቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ፕላንት ሌአውት 100% መገምገም፣
➢ በአዲስ ለሚቀርቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች 100% የማሽነሪ ዝርዝር መግለጫ ድጋፍ መስጠት፣
➢ በአዲስ የቀርቡ 400 የግብርና ፕሮጀክቶች፣ 400 የአበባ፣አትክልትና እፀ-ጣዕም ፕሮጀክቶች እና 200 የአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶች በድምሩ 1000 ፕሮጀክቶችን መገምገም፣

**5.5. ተገምግመው ላለፉት አምራች ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መሬት መስጠት፣**

➢ ተገምግመው ላለፉ 1,078 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች 591.877 ሄ/ር መሬት መስጠት
➢ ተገምግመው ላለፉ 197 የግብር ፕሮጀክቶች 6,680 ሄ/ር ፣ 159 አበባ አትክልትና ፍራፍሬ ፕሮጀክቶች 4,000 ሄ/ር መሬት እና 616 የአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶች 2000 ሄ/ር መሬት በድምሩ ለ972 ፕሮጀክቶች 12,680 ሄ/ር መሬት መስጠት፤

5.6. **የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና ሌሎች ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ወደ አፈፃፀም ማስገባት፣**

- ለ861 የአምራች ኢንዱስትሪዎች የአካባቢ እንክብካቤ ስርዓት የሚጠይቀውን ቅድመ ሁኔታ(EIA) እንዲያሟሉ ድጋፍ ማድረግ፣
- መሬት የተሰጣቸውን 861 የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ወደ ግንባታ ማስገባት፣
- ወደ ግንባታ የገቡ 839 የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን ግንባታቸውን እንዲያጠናቅቁ ማድረግ፣
- ግንባታ ያጠናቀቁ 537 የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ማምረት እንዲገቡ ፣
- 118 የግብርና ፕሮጀክቶችን፣ 130 የአበባ፣ አትክልት ፣ፍራፍሬና ዕፀ-ጣዕም ልማት ፕሮጀክቶችን፣ 585 የአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶችን በድምሩ 833 ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ **ከቅድመ ግንባታ ወደ ግንባታ ማስገባት** ፣
- 47 የግብርና ፕሮጀክቶችን፣296 የአበባ፣አትክልት ፣ፍራፍሬና ዕፀ-ጣዕም ልማት ፕሮጀክቶችን፣ 236 የአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶችን በድምሩ 579 ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጭ ያሉ ሌሎች ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ **ከግንባታ ወደ ወደ ምርት/አገልግሎት ማስገባት** ፣
- 245 የአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶችን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ **ከቅድመ ግንባታ ወደ አገልግሎትማስገባት** ፣

**5.7.** በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸዉን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችና ተቋማትን ማቋቋምና መልሶ ማጠናከር

- በጥናት የተለዩ የኢንቨስተመንት ፕሮጀክቶችን የማቋቋም እና መልሶ ወደ ስራ ማስገባት
- የተለያዩ የማበረታቻዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ
- ጉዳት የደረሰባቸውን ተቋማት በግብዓት እና ቁሳቁስ ማጠናከር

**5.8. ክፍት በሆኑ 57 የመስሪያና መሸጫ ወለሎች ኢንተርፕራይዞችን ማስገባት፣**

**5.9. በአምራች ኢንዱስትሪውና በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለረጅም ጊዜ ቦታ አጥረው የተቀመጡ ፕሮጀክቶችን በጥናት በመለየት ወደ ስራ እንዲገቡ መደገፍ፣**

- ለረጅም ጊዜ አጥረው የተቀመጡ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን በመደገፍ ወደ ስራ ማስገባት እና ወደ ስራ ባልገቡት ላይ እርምጃ መውሰድ፣

- ከአምራች ኢንዱስትሪው ውጭ የሆኑ ለረጅም ጊዜ አጥረው የተቀመጡ 178 ፕሮጀክቶች በመደገፍ ወደ ስራ ማስገባት እና ወደ ስራ ባልገቡት ላይ እርምጃ መውሰድ፣

**5.10. ለማኑፋክተሪንግ እና ሌሎች የኢንቨስትመን ፕሮጀክቶች በሚለሙባቸዉ ሳይቶች መሰረተ ልማት ማሟላት፣**

- ለኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ለኢንዱስትሪ መንደሮች፣ ለክላስተር ማዕከላትና ከኢንዱስትሪ መንደር ውጭ ላሉ የማኑፋክቸሪንግ ፕሮጀክት ሳይቶች የመንገድ፤ የመብራት፤የውሀ እና የቴሌ መሰረተ ልማት ማሟላት፣

**5.11. ምርት ላልጀመሩ፣ በማምረት ላይ ላሉ የማኑፋክተሪንግ ኢንዱስትሪዎች እና ምርት/ አገልግሎች ለጀመሩ የኢንቨስትመን ፕሮጀክቶች መሰረተ ልማት ማሟላት፣**

- 300 የመንገድ፤ 400 የመብራት፤ 150 የውሀ እና 20 የቴሌ ምርተር ያልጀመሩ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን መሰረተ ልማት ችግሮችን በመለየት መፍታት፣
- 764 አነስተኛ፣ 154 መካከለኛ እና 88 ከፍተኛ በድምሩ 1006 ምርት ላይ ያሉ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የመንገድ፤ የመብራት፤የውሀ እና የቴሌ መሰረተ ልማት ችግሮችን በመለየት መፍታት፣
- ምርት/ አገልግሎች ለጀመሩ 150 የግብር፣ 66 የአበባ፣አትክልት፣ፍራፍሬና እፀጣም እና 444 ለአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶች በድምሩ 660 ፕሮጀክቶች የመንገድ፤ የመብራት፤ የውሀ እና የቴሌ መሰረተ ልማት ችግሮችን በመለየት መፍታት፣
- የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶችን እና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በመመሪያው መሰረት የማስፋፊያ ቦታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ፣

**5.12. የዘርፍ ለውጥ የሚጠይቁ አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች አስፈላጊሆኖ ሲገኝ 100% የዘርፍ ለውጥ ማድረግ፣**

**5.13. የአምራች ኢንዱስትሪዎ ች እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ፣**

**5.13.1. የአምራች ኢንዱስትሪዎች ፕሮጀክቶችን የፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ፣**

- ለ348 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የ309.5 ሚሊዮን ብር የሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት እና ለ411 አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የ757.8145 ሚሊዮን ብር የስራ ማስኬጃ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ፣

- ለ50 ምርት ያልጀመሩ አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የ415.863 ሚሊዮን ብር የሊዝ ፋይናንስ እና ለ100 ምርት ያልጀመሩ አምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የ11736.9 የፕሮጀክት ፋይናንስ ብድር ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ፣

**5.13..2. ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሊዝ ፋይናንስ፣ፕሮጀክት ፋይናንስ እና የስራ ማስኬጃ ብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ፣**

- ለ197 የግብርና ፕሮጀክቶች 0.1388 ቢሊዮን ብር የፕሮጀክት ፋይናንስ፣ 4 ቢሊዮን ብር የሊዝ ፋይናንስ እና 0.1408 ቢሊዮን ብር የስራ ማስኬጃ ብድር
- ለ70 የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እና እፀጣም 0.7 ቢሊዮን ብር የፕሮጀክት ፋይናንስ እና 0.014 ቢሊዮን ብር የስራ ማስኬጃ ብድር
- ለ616 ለአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶች 12 ቢሊዮን ብር የፕሮጀክት ፈይናንስ እና 6.16 ቢሊዮን ብር የስራ ማስኬጃ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍ፣

**ግብ.6. የአምራች ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የማበረታቻ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመደገፍ ወደ አፈጻጸም የመግባት አቅማቸውን ማሳደግ፣**

**6.1. የማበረታቻ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን የሚጠይቁ የአምራች ኢንዱስትሪዎችና ለግብርናና የአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግና መከታተል፣**

- **የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን የጠየቁ 50 የግብርና፣ 30 የአበባ፣ ዕፀጣምና አትክልትና ፍራፍሬ እና 30 የአገልግሎት ሰጭ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍና መፍቀድ**
- **የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን የጠየቁ 20 የግብርና እና 20 የአበባ፣ ዕፀጣምና አትክልትና ፍራፍሬ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደገፍና መፍቀድ**
- **ከጉምሩክ ቀረጽ ነጻ የተፈቀዱ ማበረታቻዎች ለታለመለት ዓላማ መዋላቸዉን 605 የአምራች ኢንዱስትሪዎች እና 1841 ሌሎች የኢንቨደስትመንት ፕሮጀክቶችን መከታተልና ከታለመለት አላማ ዉጭ ያዋሉትን መረጃ በመለየት የዉሳኔ ሃሳብ ለቢሮዉ መላክ**

**ግብ.7.የአምራች ኢንዱስትሪዎችን አማካይ የማምረት አቅም ከ52% ወደ 60% ማሳደግ**

7.1. **ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣**

- የቴክኒካ ክህሎት ችግር ያለባቸውን **ለ1,299 አነስተኛ፣ለ381 መካከለኛ እና 150 ከፍተኛ በድምሩ** 1,830 ኢንዱስትሪዎች በመለየት መፍታት፣
- የኢንተር ፐርነር ሽፕ ችግር ያለባቸውን**ለ1,433 አነስተኛ፣ለ376 መካከለኛ እና 134 ከፍተኛ በድምሩ** 1,943 ኢንዱስትሪዎች በመለየት መፍታት፣
- የጥራትና ምርታማነት ችግር ያለባቸውን **ለ1,404አነስተኛ፣ለ345 መካከለኛ እና 145 ከፍተኛ በድምሩ** 1,894 ኢንዱስትሪዎች በመለየት መፍታት፣
- በበአግሮፕሮሰሲንግ 18፣ በጨርቃጨርቅ፣ አልባሳትና ቆዳ 6፣ በእንጨትና ብረታብረት ልማት 15 በድምሩ 39 ቴክኖሎጅዎችን በመቅዳት 31 ቴክኖሎጅዎችን የቴክኖሎጅ ሽግግር በማድረግ **ለ388 አነስተኛ፣ለ177መካከለኛ እና 67 ከፍተኛ በድምሩ** 1,680 ኢንዱስትሪዎች በመለየት የቴክኖሎጅ ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣

7.2. **በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ እና በሌሎች ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ያለውን የግብዓት አቅርቦት ችግር መፍታት፣**

7.2.1. **ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልግ በሃገር ውስጥ ገበያ የሚሸፈን የግብአት ፍላጎትን በመለየት መፍታት፣**

- ለ119 አነስተኛ፣ለ67 መካከለኛ እና ለ48 ከፍተኛ በድምሩ **ለ234 አምራች ኢንዱስትሪዎች** ***የ22.9 ቢሊ.ብር*** **በሃገር ውስጥ በኢንዱስትሪዎች መካከል በሚፈጠር የገበያ ትስስር** **4,537.738 ቶን** በማቅረብ የግብአት ችግርን መፍታት፣
- በኢንዱስትሪዎች መካከል ከተፈጠረ ትስስር ውጭ ለ242 አነስተኛ፣ለ115 መካከለኛ እና ለ75 ከፍተኛ በድምሩ **ለ432 አምራች ኢንዱስትሪዎች የ18.037 ቢሊ.ብር 165,780.477 ቶን** በማቅረብ የግብአት ችግርን መፍታት፣

7.2.2. **ለግብርናና አገልግሎት ዘርፎች የሚያስፈልግ ኬሚካል፣ ሲሚንቶና ሌሎች የግብአት ፍላጎትን በመለየት መፍታት፣**

7.2.3. **ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልግ በውጭ ገበያ የሚሸፈን የግብአት ፍላጎትን እና የውጭ ምንዛሬ ፍላጎትን በመለየት እንዲፈታላቸው መደገፍ፣**

- ለ246 አምራች ኢንዱስትሪዎች **በውጭ ገበያ የሚሸፈን 29,747.855 ቶን** የ244.94 ሚሊ.ዶላር ግብአት በማቅረብ የግብአት ችግርን መፍታት፣

- ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልግ 244.6944 **ሚሊ.ዶላር** የውጭ ምንዛሬ በማቅረብ የአምራች ኢንዱስትሪዎችን የምንዛሬ ችግር መፍታት፣

**7.2.4. ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጭ ላሉ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚያስፈልግ የውጭ ምንዛሬ ፍላጎትን በመለየት እንዲፈታላቸው መደገፍ፣**

- ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጭ ለሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 10 የግብርና ፕሮጀክቶች፣ 20 አበባ አትክልት፣ ፍራፍሬና ዕፀ-ጣዕም ፕሮጀክቶች እና 10 የአገልግሎት ፕሮጀክቶች በድምሩ ለ40 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚያስፈልግ 25 **ሚሊ.ዶላር** የውጭ ምንዛሬ በማቅረብ ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጭ ያሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የምንዛሬ ችግር መፍታት፣

## 7.3. አምራች ኢንዱስትሪዎችን እና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን የፐርፎርማንስ/አፈጻጸም ኦዲት እንዲያደርጉ መደገፍ፣

- 1507 አነስተኛ፣ 387 መካከለኛ እና 205 ከፍተኛ በድምሩ 2,099 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በገቡት ውል መሰረት እንዲሰሩ በመደገፍ 1,028 አነስተኛ፣ 335 መካከለኛ እና 178 ከፍተኛ በድምሩ 1,541 አምራች ኢንዱስትሪዎች በገቡት ውል መሰረት እንዲሰሩ በማድረግ ኦዲት የተደረጉ አምራች ኢንዱስትሪዎች አፈጻጸም አነስተኛ70%፣ መካከለኞች 72.5% እና ከፍተኞች 73.75% በአማካኝ አፈጻጸም 72.08 % እንዲደርስ ማድረግ፣
- አነስተኛ1,177 ፣ መካከለኛ 597 እና ከፍተኛ 226 በድምሩ 2,000 አምራች ኢንዱስትሪዎችን አመታዊ የፋይናንሻል ኦዲት እንዲያስደርጉ በመደገፍ አነስተኛ 798 ፣መካከለኛ 470 እና ከፍተኛ 207 በድምሩ 1738 አምራች ኢንዱስትሪዎች አመታዊ ፋይናሻል ኦዲት እንዲያሰደርጉ ማድረግ፣

## 7.4. አምራች ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ወጥና ሳይንሳዊ በሆነ አሰራር እንዲለኩ መደገፍ፣

- ካሉት አምራች አንዱስትሪዎች ውስጥ 50% (1166 አነስተኛ፣ 410 መካከለኛ እና 178 ከፍተኛ በድምሩ 1,754 አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍና በመለካት አማካይ የማምረት አቅማቸውን 60% ማድረስ፣

**7.5. ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን አምራች ኢንዱስትሪዎችንና ሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎችን መለየትና ቀምሮ ማስፋት፣**

- በ38 አነስተኛ፣ በ30 መካከለኛ እና በ29 ከፍተኛ በድምሩ በ97 አምራች ኢንዱስትሪዎች ተሞክሮዎችን በመለየትና በመቀመር ለ 42 አነስተኛ፣ ለ33 መካከለኛ እና ለ 32 ከፍተኛ በድምሩ ለ 107 አምራች ኢንዱስትሪዎች ተሞክሮዎችን ማስፋት፣
- በግብረናና በሆርቲካልቸር ፕሮጀክቶች 42 ተሞክሮዎች በመቀመር ማስፋት፣ በአጠቃላይ እንደተቋም በሁሉም ዘርፎች 131 ተሞክሮዎችን በመቀመር 71ዱን ማስፋት፣

**7.6. አምራች ኢንዱስትሪዎችን የደረጃ ሽግግር መስራት፤**

- 61 ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ፣ 44 ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ በድምሩ 105 የደረጃ ሽግግር የሚያደርጉ አምራች ኢንዱስትሪዎችን መለየትና መደገፍ ፣

**ግብ.8. በአምራች ኢንዱስትሪዎች እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከሚገኙ ምርቶች የሚገኝ የኤክስፖርት ገቢን ማሳደግ፣**

**8.1. ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ የሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ተጨማሪ አቅም ለመፍጠር የሚያስችል ድጋፍ መስጠት፣**

**8.1.1.ነባር ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ የሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተጨማሪ አቅም ለመፍጠር የሚያስችል ድጋፍ መስጠት፣**

- 5 መካከለኛ እና 37 ከፍተኛ በድምሩ 42 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን ተጨማሪ አቅም በመፍጠር ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ እንዲልኩ በመደገፍ 2,574.055 ቶን ለውጭ ገበያ በማቅረብ 233.43 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንዲያደርጉ ማድረግ፣

**8.1.2.ምርታቸውን ወደ ውጩ ገበያ የሚልኩ አዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተጨማሪ አቅም ለመፍጠር የሚያስችል ድጋፍ መስጠት፣**

- 17 አነስተኛ፣ 17መካከለኛ እና 34 ከፍተኛ በድምሩ 68 አዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ እንዲልኩ በመደገፍ 2 አነስተኛ፣ 10 መካከለኛ እና 22 ከፍተኛ በድምሩ 34 አምራች ኢንዱስትሪዎች

ተጨማሪ አቅም በመፍጠር 30,322.3 ቶን ለውጭ ገበያ በማቅረብ 26.89884 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንዲደርጉ ማድረግ፣

8.1.3. **በነባር አበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ዕፀ-ጣዕም ፕሮጀክቶች ምርታቸውን ወደ ውጭ እንዲልኩ ድጋፍ ማድረግ፣**

- 9 **ነባር አበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ዕፀ-ጣዕም ፕሮጀክቶች** ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ እንዲልኩ በመደገፍ 8,000 ቶን ለውጭ ገበያ በማቅረብ 35 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንዲደርጉ ማድረግ፣

**8.1.4. በአዲስ ግብርና፣ አበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ዕፀ-ጣዕም ፕሮጀክቶች ምርታቸውን ወደ ውጭ እንዲልኩ ድጋፍ ማድረግ፣**

- 1 ግብርና እና 6 **አበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ እና ዕፀ-ጣዕም ፕሮጀክቶች** ምርታቸውን ወደ ውጭ ገበያ እንዲልኩ በመደገፍ 2,476 ቶን ለውጭ ገበያ በማቅረብ 12 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንዲደርጉ ማድረግ፣

## ግብ.9. ስትራቴጂክ የገቢ ምርትን የሚተኩ የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻን ማሳደግ፣

### 9.1.ስትራቴጅክ ገቢ ምርትን የሚተኩ ምርቶችን እና ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመለየት መደገፍ

9.1.1. **ስትራቴጅክ ገቢ ምርትን የሚተኩ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን መለየት፣**

- ስትራቴጅክ ገቢ ምርትን የሚተኩ 17 በአግሮፕሮሰሲንግ፣ 17 በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአት ምርቶች፣ 8 በጨርቃጨርቅና አልባሳት እና 20 በእንጨትና ብረታብረት በድምሩ 62 ምርቶችን በመለየት ድጋፍ ማድረግ፣

9.1.2. **ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን መለየት፣**

- 36 አነስተኛ፣ 303 መካከለኛ እና 185 ከፍተኛ በድምሩ 524 ተኪ ምርት የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች በመለየት እና ድጋፍ በማድረግ የሚመረት የገቢ ምርት መጠንን መጨመር፣

9.1.3.ያዳኑትን የውጭ ምንዛሬ መጠን መለየት፣

- ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍና የምረት መጠንን እንዲጨምሩ በማድረግ 3.7784 ሚሊ ዶላር ከአነስተኞች፣ 89.5371 ሚሊዮን ዶላር ከመካከለኞች እና 166.8259 ሚሊዮን ዶላር ከከፍኞች በድምሩ 260.1414ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ ን ማዳን፣

**ግብ. 10. ከአምራች ኢንዱስትሪዉ እና ከሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚፈጠረውን የስራ እድል ማሳደግ፣**

**10.1. ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች በማጠናከርና እና ስራ ያቆሙ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ምርት በመመለስ የስራ እድል እንዲፈጥሩ ማድረግ ፣**

**10.2. ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች ተጨማሪ የስራ እድል እንዲፍጥሩበመለየት መደገፍ፣**

- 1288 አነስተኛ፣ 428 መካከለኛ እና 163 ከፍተኛ በድምሩ 1879 ነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን በማጠናከር ከአነስተኞች 4807 ፣ከመካከለኞች 2998 እና ከከፍተኞች 2724 **በድምሩ 10,529 የስራ እድል መፍጠር**

**10.3. አዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎች በመከታተል ወደ ስራ እንዲገቡ/ምርት እንዲጀምሩ በማድረግ የስራ እድል እንዲፍጥሩ መደገፍ፣**

- 213 አነስተኛ፣ 107 መካከለኛ እና 69 ከፍተኛ በድምሩ 389 አዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎችን በአዲስ ወደ ምርት ከአነስተኞች 1278 ፣ከመካከለኞች 3317 እና ከከፍተኞች 6969 **በድምሩ 11,564 የስራ እድል መፍጠር፣**

10.4. **በፕሮጀክት ደረጃ በአሉ 100 የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች 1000 ቋሚ የስራ እድል መፍጠር፣**

**11. ጠቅላላ በአምራች ኢንዱስትሪው ወንድ 11,547 ሴት 11,546 በድምሩ 23,093 የስራ እድል መፍጠር፣**

**11.1. በሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለዜጎች ቋሚ የስራ እድል እንዲፈጥሩ መደገፍ**

- ቅድመ ግንባታ ላይ ባሉ ከአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ውጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች **ወንድ 3039 ሴት 1787 በድምሩ** 4826 *ስራ ዕድል መፍጠር,*

- ከቅደመ ግንባታ ወደ ግንባታ በገቡ ከአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ውጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወንድ 9816 ሴት 6588 በድምሩ 16404 የስራ ዕድል መፍጠር፣
- ከቅድመ ግንባታ ወደ አገልግሎት በገቡ ከአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ውጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወንድ 1570 ሴት 467 በድምሩ 2,037 የስራ ዕድል መፍጠር፣
- ከግንባታ ወደ ማምረት/አገልግሎት መስጠት በገቡ ከአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ውጭ በሆኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወንድ 7747 ሴት 6518 በድምሩ 14,265 የስራ ዕድል መፍጠር፣
- ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውጭ ባሉ ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ጠቅላላ ወንድ 22,172 ሴት 15,360 በድምር 37,532 የስራ እድል መፍጠር

## 11.2. ጠቅላላ በአምራች ኢንዱስትሪዎች እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች ወንድ 33,719 ሴት 26,906 በድምሩ 60,625 የስራ ዕድል መፍጠር ፡

11.3.በአምራች ኢንዱስትሪዎች እና በሌሎች የኢንቨስትመንት ዘርፎች ከተፈጠረው የስራ ዕድል፡

- በስርዓተ ፆታ መለየት፣
- የወጣቶችን ድርሻ መለየት፣
- የአካል ጉዳተኞች ድርሻ፣

**ግብ.11. የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና ሌሎች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ምርታማነት የሚያሻሽሉ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማሳደግ፣**

11.1. ችግር ፈች የጥናት፣ምርምርና ስርፀት ስራዎችን ከከፍተኛ ትምህርት/ከቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ጋር በመቀናጀት የማከናወንና የማላመድ ስራዎችን መስራት፣

- ችግር ፈች የጥናት፣ምርምርና ስርፀት ስራዎችን ከተለያዩ ድርጅቶች እና ከከፍተኛ ትምህርት/ከቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ጋር በመቀናጀት የማከናወንና የማላመድ ስራዎችን መስራት፣

### ግብ.12. የቴክኖሎጅ ልማትና የመረጃ አያያዝ ውጤታማነትን ማሳደግ

12.1. የአምራች ኢንዱስትሪዎችን እና የሌሎች የኢንቨስትመንት መረጃዎችን /ፕሮፋያል/ 100% ወቅታዊ ማድረግ፣

- 589 አዲስ አምራች ኢንዱስትሪዎችን መረጃ እና 2,320 የነባር አምራች ኢንዱስትሪዎችን መረጃ ወቅታዊ በማድረግ ወደ ዳታ ቤዝ ማስገባት፣
- 4,364 የግብርና፣ የአበባ፣አትክልት ፍራፍሬና እፀጣም እና የአገልግሎት ሰጭ ፕሮጀክቶችን መረጃ ወቅታማድረግ፣

12.2. የተቋሙን የመረጃ አያያዝና አስራር በሚፈለገው መልኩ የማሰብሰብና የማደራጀት ስራ መስራት፣

- በአዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚወጡ 3,000 ፕሮጀክቶች መረጃዎችን በማሰባሰብ ወደ መረጃ ቋት የማስገባት
- ወደ አፈፃፀም የገቡ እና የሚገቡ 1828 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን መረጃ ቋት ላይ ወቅታዊ ማድረግ፣
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰረዘባቸውን ባለሃብቶች መረጃ ከመረጃ ቋት ማስወጣት

12.3. በቢሮ ደረጃ የክልሉን የኢንቨስተመንት ፕሮጀክቶችን መረጃ የሚያሳይ ስታቲካል መፅሄት ማዘጋጀት

## ክፍል ሶስት፡-የሰው ሃብትና ፋይናንስ ፍላጎት

ዕቅዱን ለማሳካት የሚያስፈልገው የሰው ሃብትና ፋይናንስ ፍላጎት በየበጀት አመቱ ተከፋፍሎ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ተቀምጧል፡፡

### 3.1. የሰው ሃብት ዕቅድ

<u>**የሰው ሃብት ፍላጎት መግለጫ**</u>

| ተ.ቁ | የተቋሙ ስም | አሁን ያለው የሰው ሃይል ብዛት | በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ የሚያስፈልገው የሰው ሃይል | ልዩነት | በ2015 መሟላት ያለበት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ/እስከ ወረዳ ድረስ/ | 2,266 | 2943 | 677 | 84 |

### 3.2 የፋይናንስ ዕቅድ

የፋይናንስ ዕቅድን በሚመለከት የ2015ዓ.ም. በገንዘብና ኦኮኖሚ ልማት ቢሮ የተደለደለውን የፕሮግራም በጀት ጣሪያ መነሻ በማድረግ ከመንግስት ግምጃ ቤት ለዕቅድ ዘመኑ የሚያስፈልገው በጀት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመላክቶ ተዘጋጅቷል፡

**የ2015ዓ/ም የፋይናንስ ፍላጐት ዕቅድ**

| የወጪ አይነት | መነሻ<br>በ2014 የተመደበ በጀት | በ2015 ዓ.ም የሚያስፈልግ<br>የተጠየቀ |
|---|---|---|
| **ደመወዝ** | 35,144,093.00 | 42,305,700.00 |
| **ስራማስኬጃ** | 24,446,102.00 | 34,584,682.00 |
| **ካፒታል** | 200,000,000.00 | 460,000,000.00 |
| **ድምር** | **268,000,000.00** | 536,890,382.00 |

**ክፍል 4፡- የማስፈጸሚያ አቅጣጫዎች/ስልቶች/**

- ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓትን መተግበር
- ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር
- አጋር አካላትን በላቀ ደረጃ ማሳተፍ
- ቀጣይነት ያለው የውድድርና የማበረታቻ ሥርዓትን ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ
- ጠንካራ የመረጃ ልውውጥና የሪፖርት ግንኙነትን የማሳለጥ አቅጣጫን መከተል
- መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት
- የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በትኩረት ለይቶ የመፍታት አቅጣጫን መከተል፣

**ክፍል.5. መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች**

### 5.1. መልካም አጋጣሚዎች

- የዘርፉን ልማት የሚያግዙ አመቺ ፖሊሲዎችና ስትራተጂዎች መኖር እንዲሁም በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማቅረብ የሚያስችል አቅም እየተፈጠረ መሆኑ፣

- የክልሉ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እንደ ከፍተኛ የገበያ አቅም ስለሚወሰድ እንዲሁም በምድራዊ አቀማመጧ ለበርካታ የአለም ሀገራት የኢንቨስትመንትና የገበያ መዳረሻ አገር ልትሆን መቻሏ፤

## 5.2. ስጋቶች

- የፋይናንስና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ውስንነት ሊፈጥር የሚችለው አሉታዊ ተጽዕኖ፣
- በሚፈለገው ፍጥነት የመሬትና የኃይል አቅርቦትን ማረጋገጥ ፈታኝ ሊሆን መቻሉ፣
- የአገር ውስጥ ባለሀብት በምርትና ምርታማነት እንዲሁም በምርት ጥራት በአለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን ያለው ዝግጁነት ዝቅተኛ መሆን፣
- ኮቪድ 19 በማህበራዊም ሆነ በኢኮኖሚ ላይ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽኖ እየጨመረ ከሄደሚ
- በአሁኑ ሰዓት ያለው የሰላም ሁኔታ

## 5.3. የስጋት ማስወገጃ ስልቶች

መልካም አጋጣሚዎችን አሟጦ በመጠቀም ስጋቶች የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ለመቀነስ ቀጥሎው የተዘረዘሩት ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

- የመፈፀምና የማስፈፀም ውስንነት ለመፍታት የድጋፍና ክትትል ፕሮግራምን አጠናክሮ መቀጠል፡
- የመሠረተ ልማት እና ተያያዥ አገልግሎች ላይ የሚታየውን ክፍተቶች ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ለመፍታት መሞከር፡፡
- የሰላሙን ሁኔታ በተመለከተ ለክልሉ ማህበረሰብ በኢንዱስትሪዎች ላይ የሚደርስ ጉዳት የህዝቡን ጥቅም የሚያስቀር መሆኑን ግንዛቤ መፍጠር፣ የፀጥታ አካላት ከመቸውም በተለየ መልኩ ኢንዱስትሪዎች ላይ ትኩረት ሰጥተው ጥበቃ እንዲያ ደርጉ እና ለህዝቡ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እንዲሰሩ ማድረግ፣ 7

## ክፍል.6.የክትትልና የግምገማ ስርዓት

የተዘጋጀው የአስር ዓመት መሪ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በየበጀት ዓመቱ የተቀረጹ ግቦች ለማሳካት በሚቀመጡ አመልካቾች መሰረት ክትትልና ግምገማ ይደረጋል፡፡

የ5 ዓመቱ መሪ ዕቅድ መሰረት በማድረግ በሚፀደቀው ዓመታዊ ዕቅድ ተቋሙ ፣ ተጠሪ ተቋማት የሥራ ኃፊላዎች እና አጋር አካላት በየጊዜው የቅርብ ክትትል እየተደረገ፣ ወርሃዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እንዲዘጋጅ ተደርጎ በየተቋማቱ የበላይ አመራር ሰብሳቢነት በሥራ አመራር ደረጃ ይገመገማል፡የዘርፉ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ ዓመት፣ የዘጠኝ ወራትና ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በማዘጋጀት በዘርፉ የበላይ አመራር ሰብሳቢነት ሥራ አመራር እና በጠቅላላ ሠራተኛ

እንዲሁም እስከ ወረዳ ድረስ ባሉ በሚመለከታቸው አካላት፣ በኢኮኖሚ፣ንግድና ከተማልማት ቋሚ ኮሚቴ ግምገማ የሚደረግ ሲሆን የሚሰጡ ግብረ-መልሶች እና የሥራ አቅጣጫም ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 6.1. የሪፖርት አቀራረብ

ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ አኳያ ከተቀመጡ ግቦች አንጻር የግምገማ ሪፖርት ሲዘጋጅ የዘርፍ ቁልፍ አፈፃፀም የውጤት አመልካቾች (Output Indicators) እና የስኬት አመልካቾች (Outcome Indicators) ታሳቢ ባደረገ አግባብ የሚፈፀም ሆኖ የሪፖርት አቀራረብ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| የዘርፉ መጠሪያ | የስራው ባለቤት መጠሪያ | |
|---|---|---|
| የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚሸፍኑት ጊዜ | የሪፖርቱ ይዘት | ሪፖርቱ የሚቀርብለት አካል |
| አመታዊ | ለስኬቶች እና ውጤቶችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን፣ የበጀት ውጤታማነትን፣ የኦዲት እና የለውጥ፣ የመልካም አስተዳደርና የሰው ሀ/ስ/አመራር ጉዳዮችን ማካተት አለበት፡፡ | ለሚመለከታቸው ፌደራልና የክልልተቋማት፣ለኢኮኖሚ፣ንግድና ከተማ ልማት ቋሚ ኮሚቴ |

| የዘርፉ መጠሪያ | የስራው ባለቤት መጠሪያ | |
|---|---|---|
| የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚሸፍኑት ጊዜ | የሪፖርቱ ይዘት | ሪፖርቱ የሚቀርብለት አካል |
| ስድስት ወራት | ለስኬቶች እና ውጤቶችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን፣ የበጀት ውጤታማነትን፣ የኦዲት እና የሰው ሀ/ስ/አመራር ጉዳዮችን ማካተት አለበት፡፡ | ለሚመለከታቸው ፌደራልና የክልልተቋማት፣ለኢኮኖሚ፣ንግድና ከተማልማት ቋሚ ኮሚቴ |
| በየሩብ ዓመት | ለስኬቶች እና ውጤቶችን ያካትታል፡፡ በተጨማሪም የበጀት አፈፃፃም ውጤታማነት እና የሰው ሀ/ስ/አመራር ጉዳዮችን ያካትታል፡፡ | ለሚመለከታቸው ፌደራልና የክልልተቋማት፣ለኢኮኖሚ፣ንግድና ከተማ ልማት ቋሚ ኮሚቴ |

6.2. የግምገማ ስርዓት

በዘርፉ የሚዘጋጀው ሪፖርት ከላይ የተጠቀሱትን የአመልካች አይነቶችን ታሳቢ በማድረግ ግምገማው የሚያተኩርባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች፡-

- የዘርፉ የፊዚካል አፈፃፀም፣
- የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ማለትም፡-
    - ✓ የስርዓተ-ፆታ
    - ✓ የወጣቶች እና የሴቶች
    - ✓ ኤች አይ ቪ/ኤድስ
    - ✓ አካል ጉዳተኞች እና
- የዘርፉ የበጀት አፈፃፀም፣
- የዘርፉ ኦዲት አፈፃፀም፣
- የተቋማዊ ለውጥ፣ መልካም አስተዳደር እና ሰው ሀብት ስራ አመራር አፈፃፀም፣

ላይ በማተኮር የዘርፉ ቁልፍ የውጤት መስክ ለማሳካት የሚከናወኑ ቁልፍ ተግባራትን አፈጻጸም ለመከታተልና ለመገምገም በሚያስችል አግባብ የዘርፉ የበላይ አካልም ሆነ በየደረጃው ያለ አመራር ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ተግባር ነክ አመልካቾች ላይ የቅርብ ክትትል በማድረግና የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በመፍታት ለቁልፍ የውጤት መስኮች ያላቸውን አስተዋፆ በማሳደግ ውጤታማና ተፈፃሚ መሆናቸውን በማረጋገጥ ግምገማው የሚከናወን ይሆናል፡፡